## የእስልምና ማኅበራዊ ተቋማት

> በ1966 ዓ.ም ድርቅ ስለነበር በርካታ ሰዎች ተሰደዱ።

እኛ ተርቲም (ጠርጥም) የሚባል አለን፤ ይህም ማለት ሴቶችም ወንዶችም በየቀኑ ወደ መስጊድ ይሄዱና ወንዶቹ በአንድ ረድፍ፤ ሴቶቹ ደግሞ በሌላኛው ረድፍ ተቀምጠው ቡና በማፍላት፤ በአንድ ላይ ቁርስ በመብላት ፤ ኑብዩን በማወደስና በመዐለይ ከቆዩ በኋላ በፍፃሜው ተመራርቀው የሚለያዩበት ነው። ሰው ከሞተ ገንዘብ አዋጥተን በቀብር ጊዜ የምንረዳዳበት ቅሬ አለን።

በወረዳ ደረጃ የእስልምና ኰሚቴ ኃላፊ ነኝ። ቀደም ሲል የሶስት ወረዳ ቃዲ በመሆን አገልግያለሁ። አሁን አውራጃ የሚለው የአስተዳደር ክፍፍል በኢህአዴግ ስለታጠፈ በምኖርበት ወረዳ ቃዲ ነኝ። በተሰጠኝ ኃላፊነትም ከባሎቻቸው ጋር የሚጣሉ ሴቶችን ማስታረቅ ፤ አዳዲስ ጋብቻዎችን ማስፈዐም ፤ የፍቺና የውርስ ጉዳዮችን መመልከት እና ሌሎችም ኃይማኖታዊ ተግባራትን መሥራት ነው።

ከጠርጥም ያለው ልዩነት ፤ የአባላት ሙብዛት ፤ ለቁርስ የሚዘጋጀው ዳቦ በትልቅ መጋገሪያ መሆኑ ብቻ ነው። ችግር ካለ ከቡና በኋላ እንወያያለን። ዘመድ የሌለው እንግዳ ከመጣ ደግሞ ከእኛ ጋር ቡና ጠጥቶ ፤ ቁርስ በልቶ ስለሚሄድ ጥሩ ሁኔታን ይፈጥርለታል።

በመስጊድ ለድሆች ቡና ፤ ቁርስ ከማቅረባችን በላይ ኃይማኖታችን የሚያዘውን ከገቢያችን አንድ አስረኛ የሚሆነውን ለአቅመ ደካሞችና ለአካለ ስንኩላን እንመዐውታለን። ይህን ገንዘብ

ለራሳችን ማድረግ በጥብቅ የተከለከለ ነው። የዚህ አይነቱ ትብብር አሁንም ያለ ነው።

<u>የጋብቻ ግንኙነት</u>

የጋብቻ መመሪያችን ቅዱስ ቁርአን ነው። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ ጋብቻ ከፈፀሙ በኋላ ትተው የሚጠፉ አሉ። በዚህ ጊዜ በሚፈጠረው ሁኔታ ሴቶች ችግር እየገጠማቸው ስለሄደ አንዳንድ ዋስትና የሚሆኑ ነገሮችን እያመቻቸን ነው። ድሮ ባል ሚስቱን ጥሎ ከኮበለለ ተመልሶ መጥቶ ካልፈታት በስተቀር ሌላ ትዳር ለመመስረት አትችልም ነበር፣ አሁን ግን ከመሄዱ በፊት ፈትቷት እንዲሄድ እየተደረገ ነው።

ድሮ ሴቶች ዘጠኝ ወይንም ከዚያ በላይ ካልሆናቸው፣ ወንዶች ሀያ ወይንም ሃያ አንድ አመት ካልደረሱ ጋብቻ እንዲያደርጉ አይፈቀድም ነበር። ዛሬ ግን ሴቶች ሰባት ወይንም ስምንት ዓመት፣ ወንዶች አሥራ ስድስት ወይም አስራ ሰባት ዓመት ከሆናቸው ሊያገቡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ሴቷ ለአካለ መጠን ካልደረሰች ወንዱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳያደርግ በጥብቅ ይከለከላል።

ጥንት ልጆች ሽማግሌዎችንና ወላጆቻቸውን ስለሚያከብሩ ጋብቻ የሚፈጽሙት ወላጆቻቸውን በማማከር ነበር። አሁን ግን ልጆች ወላጆቻቸውን ስለማያከብሩ የወላጆቻቸውን ፈቃድ ሳያገኙ ይገባሉ።

## የመኖር ዘዴዎች

በ1966 ዓ.ም ድርቅ በመከሰቱ ብዙ ሰዎች ወደ ጉጃምና ጉንደር ተሰደው ለአንድ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ተመልሰዋል። በዚያን ጊዜ መንግስት እርዳታ ሰጥቶ የሕዝብን ህይወት እንዲያተርፍ ለመጠየቅ እኔና ሌሎች ሰዎች ሆነን ወደ ደሴና አዲስ አበባ ሄደን ነበር። በ1974 እና በ1975 እንዲሁ ድርቅ ተከስቶ ነበር። በ1985 ዴይሪ የተባለ ተባይ ተከስቶ ሰብላችንን አወደመው። በምግብ ዕጥረት ምክንያት ሰዎች በድጋሚ ተሰደዱ። በሽታና ዕርዛት በርካታ ሰዎችን ጨረሰ።

ድርቁ የምግብ እጥረት እንዲኖር ፣ እርሻ እንዳይታረስ በማድረጉ ችግር ስለተፈጠረ ሰዎች አቅማቸው እየተዳከመ በመሄዱ ስራ ሰርተው ገቢ ለማግኘት አላስቻላቸውም ነበር። እህል ገዝተውም እንዳይመገቡ የገንዘብ አቅም አልነበራቸውም።

በ1966 በተከሰተው ረሃብ ጊዜ ሚስትም ፣ ልጆችም አልነበሩኝም። በ1985 ግን አግብቼ ልጆችም ነበሩኝ። በዚህን ጊዜ በከተማ ከሚኖሩት ዘመዶቼ እርዳታ በማግኘቴ አልተሰደድኩም። የክረምቱን ወራትም ጉመን በጨውና በዘይት እያበሰልን በመብላት ችግሩን ተወጥተነዋል። የተሰደዱት ደግሞ የቀን ስራተኛ በመሆን ፣ የሽመና ስራ በመስራት ኑሮአቸውን ሲገፉ ቆይተው ዝናብ ሲጥል ወደ ቦታቸው ተመልሰዋል። የቀሩት ሰዎችም ዝናብ ሲጥል እህል ዘርተው ጠብቀዋቸዋል። ሕብረተሰቡ ያለችውን ትንሽ ነገር በመከፋፈል እርስ በእርሱ በመረዳዳት ችግሩን አሳልፏል።



<<በአሁኑ ጊዜ ትምህርት የእናቶችና የልጆችን ኑሮ አሻሽሏል>>

[በ1966]... ከመንግስት እርዳታ ይገኛል ብለን ጠብቀን ነበር። እርዳታው ሳይመጣ ሲቀር ሰዎች ወደ መቀሌ በመሄድ በሽመና ስራ ተሰማርተው እየሰሩ የሚያገኙትን ገንዘብ ወደ ቤታቸው እየላኩ ልጆቻቸውን ይረዱ ነበር።

በ1985 መንግስት እርዳታ አድርጉልናል። በደርግ ጊዜ እርዳታው የተሻለ ነበር። ይህ ባይሆን ኖሮ ብዙ ሰው ያልቅ ነበር። እርዳታ የሚሰጠውም የሰው ሕይወት ለማትረፍ ሲባል ነበር። አሁን ግን የሚሰጠው እርዳታ በቂ አይደለም። አንድ ሰው ከብት ማለትም አንድ በሬ ወይም አንድ ላም ወይም አንድ ፍየል ካለው ዕርዳታ አይሰጥም። አንድ ትንሽ ዶንያ እህል ለአራት ሰዎች ስለሚሰጡ ይህ

ደግሞ እርዳታውን ለመቀበል በመንገዱ ላይ እያሉ እንኳ ሊመግባቸው አይችልም። ቀሪዎቻችን ደግሞ ምንም አናገኝም።

<u>ዘውዴ</u> ኢትዮ. 4

በቃለ መጠይቅ አቅራቢው እይታ የ38 ዓመቷ ዘውዴ ቃለ መጠይቁን በደስታ የመለሰች ቢሆንም <<የፊቷ ገጽታ በኑሮዋ ደስተኛ አለመሆኗን ያመለክት ነበር>> ለመነጋገር ዐጥታ ቦታ መርጠው ተቀመጡ። ከዚያም ዘውዴ አንድ ጌቲን የሚባል ሥር መዛ አውጥታ ትኩር ብላ እየተመለከተች <<ታያለህ ፤ ብዙ ህይወት ያተረፈው ይህ ሳር እንኳ ሳይቀር ደርቋል፤ ይሁን እንጂ ይህ ነበር ሰዎቻችን እየተመገቡ የቆዩት>> አለች። ረሃብ ትንሽ ትልቅ ሳይል እየመደመደው ነው ። የተከሰተው የምግብ እጥረት በይፋ ከተነገረው በላይ መሆኑን በመግለጽ ታስጠነቅቃለች።

የሕዝብ ቁጥር ጨምሯል፤ ጊዜውም የጭካኔ ጊዜ ነው። አምቻዎች እርስ በርስ ይጣላሉ፤ በእናቶችና በልጆች መካከል ስምምነት የለም፤ ኢየሱስ ክርስቶስም ከመሬት ጋር አብሮ ከድቶናል፤ እህሉም በጠራራ ፀሃይና በውርጭ ወድሟል በማለት ታማርራለች። አባቶቻችን በሚኖሩበት ጊዜ በአንድ ሾር መሬት ላይ አንድ አቁማዳ እህል ይገኝ ነበር። አሁን ግን አንድ ቁና እንኳ አይገኝም። አሁን ያለንበት ወር ፀሐይ የሚበዛበት ፤ የተዘራው እህል ደርቆ የሚታይበት፤ ለሰውም ሆነ ለእንስሳት የምግብ እጥረት ያጋጠመበት ፤ ከብቶች በመኖ እጦት እየረገፉ ያሉበት ነው። ፀሐይ ስላጠፋው የጌቲን ሥር እንኳ የለም፤ ሰው የሚበላው አጥቷል።



ልማት

ከዚህ ከባድ ዐሐይ ተርፎ የቆየውን አዝርዕት ደግሞ የጥቅምት ውርጭ ያጠፋዋል። ዘመናችን የብላ ተባላ ዘመን ሆኗል። አገሩ መለወጡን ሁሉም ሰው ያውቀዋል።

ሕዝብ እያደገ በመሄድ ላይ ነው ለማለት ካስቻሉኝ ምክንያቶች አንዱን ብጠቅስ አንዲት ልጃገረድ የጋብቻ እድሜዋ ሲያልፍ የራሷን ጉጆ ሠርታ ብቻዋን መኖር ትጀምራለች። በዚህን ጊዜ አንድ ሃብት ያለው ሰው ይመጣና ቅምጥ በማድረግ ሚስቱ ሳታውቅ ሦስት አራት ልጆችን ይወልድባታል፤ ሚስቱ ታማኝ አለመሆኑን ስትረዳ ቅምጡ... ከእሱ መውለዷን ቀርቶ ስሙን እንኳ እንዳታነሳ ያስጠነቅቃትና ትቷት ይጠፋል። በዚህን ጊዜ ልጆች የሚበሉት ሲያጡ ሌላ ሰው እንድትይዝ ስለምትገደድ ሌላ ተጨማሪ ልጅ ትወልዳለች። ልጆቹም ተገቢውን የእናት እና የአባት ፍቅር ሳያገኙ ያድጉና የሰው ቤት አገልጋይ ፤ የሃብታም ሎሌና ገረድ ይሆናሉ። አባታቸው በስደት ሄዶ ይሞት ይሆናል። ልጆቹም ተለያይተው በድህነት እየተቆራመዱ ከእናታቸው ጋር ተመልሰው ሳይገናኙ ይሞታሉ።

## የልማት ድጋፍ

ኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል ሰዎችን ለልማት እያስተባበረ ሥልጠና በመስጠት በአነስተኛ ወለድ ብድር በማበደርና የእፀዋት ዘር በመስጠት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው። ይህም ሆኖ እፀዋቱን ሳናቋርጥ ውሃ እያጠጣን ብንከባከብም ቀን ዐሐዩ፤ ሌሊት ደግሞ ውርጩ እያጠፋቸው ነው። መንግስትም ቢሆን እየተባበረን ነው፤

መሬቱ ግን ምርት አልሰጥ ብሏል። ኤስ.ኦ.ኤስ ሳህልም ልዩ ልዩ የድንች ዘሮችን እየሰጠን ነው። የምንጣፍም አሠራር ሥልጠና አግኝተናል፤ ድርጅቱ ምስጋና ይግባውና አራት የእህል ወፍጮዎችን ስለተከለልን ሴቶች ተንበርክከው በድንጋይ ወፍጮ ትንሽ እህል ለመፍጨት ያባክኑት የነበረው ጉልበትና ጊዜ ለመቆጠብ አስቾሏቸዋል። ኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል ላሞችን ፤ በጐችንና ዶሮዎችን በመስጠት እየረዳን ነው።

> ዘመናችን
> <<እርስ በእርስ
> የሚያባላ>>
> እየሆነ ነው።

ትምህርት ቤት ተሰርቶልናል። የጤና አገልግሎት መስጫ ባይኖረንም ሠልጥነው እያሰለጠኑን ያሉ የልምድ አዋላጆችን ለማግኘት ችለናል። ደገዛ፤ ጼይሪና አንበጣ የሚባሉ ተባዮች ነበሩ። ደገዛ ዝናብ ካልጣለ ስለማይጠፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግንዶችን ያጠፉል። አሁን ግን የግብርና ቢሮው የተባይ ማጥፊያ መድሃኒት በመርጨት ተባዮችን እያጠፉ ነው።

ምናልባት የተማሩ ሰዎች ከመጡና ልጆቻችንም ተምረው የተማረው ቁጥር እየጨመረ ከሄደ ሁኔታዎች ይለወጡ ይሆናል።

## ሠርግና ጋብቻ

ድሮ ሠርግ ሊሆን ሲል ጠላው ከሠርጉ አስራ አምስት ቀን ቀደም ብሎ ይጠመቅ ነበር። ልጆች ማታ ማታ ከሙሽሪትና ከሙሽራው ቤት እየሄዱ እስከ ሰርጉ ቀን ድረስ ይዘፍናሉ። እዚያው እያደሩ፤ ይበላሉ፤ ይጠጣሉ። አሁን ግን የባለሠርጐች ድግስ ያልቅባቸዋል ስለሚባል ልጆች አይሄዱም። ወደ ሠርጉም ስትሄድ

አምስት ወይንም የተቻለህን ያህል ብር ይዘህ በመሄድ ስጦታ አድርገህ ተመልሰህ መምጣት ነው። ደጋሹ ድግስ አዘጋጅቶ ሊጋብዝ የሚችለው ሰባት ወይንም ስምንት ሰዎች ስጦታ ካደረጉለት ብቻ ነው። ካልሆነ ግን ሊደግስ አይችልም። ድሮ የአንድ ሃብታም ልጅ ስትዳር ለሃያ ቀናት ያህል የምትቀመጥበት ጫጉላ ቤት ተሰርቶላት ፣ ሰንጋ፣ የበግ ወይም የፍየል ሙክት ፣ ዶሮ እየታረደ ሙሽራውና ሙሽሪት ይቀለቡ ነበር። ጓደኞችና ዘመዶች የሆኑትም የጠላ ፣ የምግብ ፣ የሙሽሮች ገላ አጣቢነት ሥራ ኃላፊ እየሆኑ ግልጋሎት ይሰጡ ነበር። ዛሬ ግን ሙሽራውና ሙሽሪት ሦስት ቀን እንኳ አይቆዩም። ከሦስት ቀን በኋላ ሙሽራዋን ከማሳ ላይ ታያታለህ። በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰው እና አናሳ የምግብ እህል ነው ያለው። በድሮ ጊዜ ለሙሽሪት እንዲህ እየተባለ ይዘፈን ነበር።

የእኛ ሙሽራ ኩሪባቸው ኩሪባቸው
በእንግሊዝኛ አናግሪያቸው
የመለያችን ጊዜ ደረሰ
ጫማዋ መልዕክት አደረሰ።

ዛሬ ግን <<እጅዋን ይዘህ አስገባት፣ እጅዋን ይዘህ አስገባት>> እያለ ነው። ምንም የማይገባን ጉዳይ ነው። በድሮ ጊዜ ሙሽራው እኔ እኮ የእንቶኔ አማች ነኝ እያለ ይኩራራ ነበር። አሁን ግን ሙሽራው በልብስ ተጀቡኖ በትዕቢት ከአማቱ ፊት ለፊት ይቀመጣል። ትዕዛዙንም አያከብርም። በድሮ ጊዜ ግን እናት ያበላሸችውን አማት ይቀጣዋል ይባል ነበር።

> ዛሬ ከእጅ ከድንጋይ ወፍጮ ተላቀናል።

<<እኩልነት ጥሩ ነው>>

ዛሬ አሳዳሪዋ የሆነውን ባሏን የምትፈራ ማንም የለችም። እኩልነት ጥሩ ነው። ዛሬ የባሏ አባትም ቢሆን ቢናገራት መልሳ በድፍረት ፊት ለፊት << አንተ ባሌ አይደለህም፤ የሚያገባህ የለም>> ብላ ትናገራለች። ድሮ በማዕድ ቤት ብቻ ተወስነው ይኖሩ የነበሩት ፣ ማንበብና መጻፍ ችለዋል። ከእጅ ወፍጮም ተላቀዋል።

ዛሬ ትምህርት ከእርሻ የተሻለ ነው። በድሮ ጊዜ መሬት እንዲያርስ፤ ድርቆሽ ለከብቶች እንዲሸከም ይጠየቅ ነበር። የድሃ ልጅም የሀብታም ሎሌ በመሆን ከብቶቹን እየጠበቀ ፣ በቅሎችን እየተከተለ ይውልና ማታ ሲመለስ ጌታውን ቆሞ ራት ያበላ ነበር። ዛሬ እኩልነት አለ። መሬቱ ግን ምርታማ አይደለም። አንድ ሴት አማቶቿን ተሳድባ ለፍች ብትዳረግ ንብረቷን ተካፍላ ልጆቿን ለባሏ ትታ በመሄድ ከፈለገች ሌላ ታገባ ነበር። ዛሬ ከልጆች በስተቀር የሚካፈሉት ንብረት እህል ወይም ከብት የለም።

ድሮ አንድ ሰው ፍቅረኛ ለማግኘት አገናኝ ፈልጎ የብር ስጦታ በማድረግ ይተዋወቅና በፍቅር አይን እየተያዩ ምንም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳያደርጉ እስከ አንድ አመት ያህል ይቆዩ ነበር። ዛሬ ግን ቀድመው ለመሳሳም ይሮጡና እናቶች ዲቃላቸውን ይሸከማሉ። ለዚህም ነው ህዝብ በፍጥነት እየጨመረ የሄደው። ድሮ አንድ ሰው ሚስት ሲፈልግ የወላድ ዘር መሆኗን ፣ ልጆች እንዳሏት ጠይቆ ካጣራ በኋላ ያገባታል። ምክንያቱም ማርና ቅቤ ከተመገቡ ልጅ አይወልዱም ተብሎ ስለሚታመን ይህን ለማጣራት ነበር ጥያቄው የሚቀርበው። ማርና ቅቤ መሃን ያደርጋል ተብሎ ይታመን ነበር።

በአሁኑ ጊዜ ሴቶች ሲወልዱ አሥር ቀን እንኳ ሳይታረሱ ልብሳቸውን ለብሰው ይነሱና አጥንታቸው እየተቆጠረ መንተል መንተል ይላሉ። እንደ ድሮው ለአርባ ቀን ስለማትታረስ መልሳ በአርባኛ ቀኗ ትፀንሳለች። ከድሮው በተለየ መልኩ በአሁኑ ጊዜ የሚፈለጉት መሃን ሴቶች እየሆኑ ነው። ወላድ ሴት ካገባም እንዳትወልድ በመፈለግ ወንዱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማቆም ሴቷን ያገልላታል። ብዙ እየወለደች ከሄደችም ለፍች ያደርሳታል። ይህን ስታይ ሴቶች በአሁኑ ጊዜ ተጨቁነዋል ያሰኛል።

## በኀብረተሰቡ መካከል ያለ እንክብካቤ

አካለ ስንኩላንን ፣ አዛውንቶችን፣ ረዳት ዘመድ የሌላቸውን ተራ በተራ እየመገቡ ፣ እያለበሱ ነበር አባቶቻችን የሚደግፏቸው። ስለሆነም ድሆችና አዛውንቶች ወይም አካለ ስንኩላን፣ ስምንት ቀናት ወይም አንድ ወር ያህል በአንዱ ቤት ፣ ቀጣዩን ወር ሌላው ቤት በመሄድ እስከ ሕይወታቸው ዘመን ድረስ እንክብካቤ ይደረግላቸው ነበር። በሞቱ ጊዜም ለከፈናቸው ሀብታም ካለ እርሱ ገዝቶ ከሌለ ደግሞ የገንዘብ መዋጮ ተደርጐ ከፈን ይገዛና የቀብሩ ስነ ሥርዓት ይፈፀማል። ስለሆነም ልጅ አልባ የሆኑና አካለ ስንኩላን በእርጅና ጊዜያቸው ገዘም ተብለው አይተውም ነበር። አሁን ግን እንኳንስ ዘመድ የሌለው ቀርቶ ዘመድ ያለው እንኳ ቢሆን ማንም ዘወር ብሎ የሚመለከተው የለም።

> አባቶቻችን አቅመ ደካሞችን ይደግፉሉ።

## የጤና መጓደል

[ድሮ] በሽታዎች ቀሳፊ አልነበሩም… አሁን አዲስ በሽታ [ሳንባ ነቀርሳ ] የሚሉት ሐኪሞች መከላከል ያልቻሉት፤ ሰውነትን አመንምኖ የሚገድል አስቀያሚ በሽታ አለ። እንዲሁም የትላልቆችንም ሆነ የልጆችን ጉሮሮ አቁስሎ ፤ ጆሮአቸውን አሳብጦ የሚያሰቃይ በሽታ መጥቷል። በቅርብ የመጣው እጅል እየተባለ የሚጠራው ደግሞ ታማሚውን በትውኪያና በተቅማጥ የሚያጣድፍ ነው። አስታማሚዎችም ተስፋ ስለሚቆርጡ በሽተኛው ቶሎ እንዲሞትላቸው ይማፀናሉ። ሲሞትም አያለቅሱም። እንዲሁም አንድ ሰው በበሽታው ከተለከፈ ከሰባት እስከ አስር የሚሆኑት የቤተሰብ አባላት ይታመሙና ይሞታሉ። ሌላው ደግሞ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚመጣ ኤድስ እየተባለ የሚጠራ በሽታ የብዙ ሰዎችን ሕይወት አጥፍቷል። በድሮ ጊዜ ሰዎች ወደ አመንዝራነት ለመግባት አይቸኩሉም ነበር፤ የነበሩትም በሽታዎች ቂጥኝና ባንቡሌ ብቻ ነበሩ። ሰዎች በቂጥኝ መያዝን ስለሚፈሩ እንዲህ እያሉ ይዘፍኑ ነበር።

ቂጥኝ ባይኖር ኖሮ
ባንቡሌ ባይኖር ኖሮ
ሸዋ ቆንጆ ነበር ለኑሮ

በዚህ የተነሳ ሰዎች ከአመንዝራነት ታቅበው ነበር። ዛሬ ግን ይህ ቀሳፊ በሽታ እያለ ወጣቱም ሆነ ትልልቁ ሰው ከአመንዝራነት አልተቆጠቡም። ሀኪሞችም በሽታውን ሊያድኑት አይችሉም። ሕዝቡ

ቢጨምርም ረሃብና ተቅማጥ ብዙ ሰዎችን እየገደለ ነው። ለመታከሚያ የሚሆን ገንዘብም የላቸውም። ዶክተሮች ለአሰሳ በሰፈራችን ከመጡ በበሽታና በረሃብ ተቆራምዶ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የማይገኝበት ቤተሰብ የለም። በአንዳንድ ቤቶችማ ለታመሙት የቤተሰብ አባላት ውሃ የሚያቀርብላቸው እንኳ የለም።

## <u>ረሃብ</u>

> አሁን ዋናው በሽታ ረሃብ ነው።

በዚህ አመትም ድርቅ ገብቷል። ሰውም ሆነ እንስሳት በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ ናቸው። እህልም ከመሬት እንደበቀለ ደርቋል። በ1984 መንግስት የረሃቡን መግባት ስላወቀ የእርዳታ እህል ተረጂዎች ወደ ተሰበሰቡበት ቦታ በተሽከርካሪዎች በመላክ ብዙ ሕይወት ለማዳን ተችሏል። ዛሬም በመንግስት ያልታወቀ ረሃብ ገብቷል። ከነጋዴዎች፣ ገንዘብና ጉልበት ካላቸው በስተቀር እንደ 1984 ያለ ረሃብ ገብቶ ሕዝቡን እያሰቃየው ነው።

[በ1984] ከመንግስት እርዳታ አግኝተን ነበር። ልብስ፣ ብርድ ልብስ፣ ወተት፣ ብስኩት፣ የምግብ ዘይት፣ ስንዴና የስንዴ ዱቄት፣ ሳሙና፣ መድሃኒት ነበር ለልጆቻችን የተሰጠን። ሕፃናቱም በየወሩ እየተመዘኑ ክብደታቸው ይታወቅ ነበር።ኮሌራም ገብቶ ብዙ ሰዎችን

> ብርሃኑ (ወንድ፣ 70 ዓመት)፣ ፍላቂት የሚኖር፣ ኢትዮ 5
> ዘመዶቻችንን ለመጠየቅ ሦስት አራት ደብሮችን አልፈን እንጓዝ ነበር፣ ስንለያይ ተሸኛኝተን፣ ተሳስመን እየተላቀስን ነበር። አሁን ግን የደረስንበት ዘመን ስንገናኝ ፊታችንን አጥቁረን የምንሄድበት ነው። ለሰላምታችን መልስ አናገኝም። የምንሠራው የጨካኞች ሥራ ነው።

ይገድል ስለነበር ፣ መንግስት የሕክምና እርዳታ በማድረግ ብዙ ሕይወትን አትርፏል። አሁን ግን መንግስት የ1984 አይነት ረሃብ መግባቱን አላወቀም መሰለኝ ትውኪያና ተቅማጥ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል። በመሬት ያለውም እህል ተሰብስቦ ወደ ጉተራ የሚገባ አይሆንም። ገና ቡቃያ እያለ ደርቋል። የተረፈውንም ውርጭ አጥፍቶታል። ዛሬ አረንጓዴ ሆኖ የምታየው ነገ ደርቆ ይታያል። ሕዝብ እያለቀ ስለሆነ መንግስት አስፈላጊውን እርዳታ ማድረግ ይኖርበታል። ባለፈው ጊዜ እርዳታ እየተቀበልን በነበርንበት ወቅት አዝመራው ሲያንሰራራ የዘፈን ግጥም ተገጠመ፣ እንዲህ ይላል፣

እንዴት ብለሽ 1984ን ረሳሽው
ማሽላ ሸጠሽ ግሽርጥ የገዛሽው

አሁን ዋናው በሽታ ረሃብ ነው፣ ትንሽ ትልቁ አልጋ ላይ ወድቋል።

***ሀምዛ*** ኢትዮ.10

ሀምዛ 28 ዓመት እድሜ ያለው እስላም ነው።

ትምህርት አለመማር ጉዳት እንዳለው ይናገራል፣ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ ወስኗል። እርሱ በሚኖርበት [ጉሚር] እየተባለ በሚጠራው ሰፈር ሬዲዮ፣ ስልክ፣ ያለው አንድም ሰው ባለመኖሩ ህብረተሰቡ ተገልሎ እንደሚኖርና ስለመሻሻልም ሆነ ስለ ራሳቸው ልማት ለመወያየት አዳጋች እንደሆነ ይሰማዋል።

በአባቶቻችን ዘመን የህዝብ ብዛት አነስተኛ ነበር... ይሁን እንጂ ሳይቆይ ብዙ ሕፃናት በመወለዳቸው የህዝቡ ብዛት ጨመረ፣ ለቤተሰብ አባላት እየተከፈለ ስለሚሠጥ መሬትም እያነሰ መጣ።

ልጆች ወላጆቻቸውን ተከትለው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ በአዲስ አካባቢ እየሰፈሩ ነው። መሬቱ እየተጣበበ መጥቷል። የቀረውም ቢሆን በጉርፍ እየተበላ ነው። ድሮ ልጆች እስኪያድጉ ድረስ ከወላጆቻቸው ጋር ይኖሩ ስለነበር ፣ ለራሳቸው መኖሪያ አይሠሩም ነበር። አሁን ግን አንድ ሰው ብቻ እስከ አራት ቤት ስለሚሰራ ዛፎች እየተቆረጡ ይወድማሉ። እኛው ራሳችን ነን አውዳሚዎቹ።

ድሮ ጅረቶች እንዳልነበሩ ይነገራል። ከጨርቆስ ስንመጣ ተሻግረነው የመጣነውን ትንሽ ጅረት አይተኸዋል? ይህ ቦታ ሳር የለበሰ እንደነበር አስታውሳለሁ። አሁን ግን ውሃ በልቶት ይታያል። ቀደም ሲል ቦታው የአንድ ገበሬ ነበር፣ እርሱ ሲያርሰው በመሬቱ ድንበር ለጉርፍ መከላከያ የሚሆን ቦታ በሳር እየተሸፈነ ትቶ ቀሪውን ያርስ ነበር፣ አሁን እርሱ መሬቱን ለጋራ አራሽ ስለሰጠው ሰውየው መሬቱን ምንም ለጉርፍ መከላከያ የሚሆን ሳይተው ሙልጭ አድርጎ ስላረሰው ውሃው መሬቱን መሃል ለመሐል በመቦርቦር እየበላው ሄደ። ይህን በደንብ የማስታውሰው ነው። ነገ ተሻግረን ስንሄድ አሳይሃለሁ፣ በሌሎች ቦታዎች ወንዝ የነበረበት አሁን ደልዳላ ቦታ ሆኗል።

## አንጥረኞች <<እንደ ቡዳ>>

[አንጥረኞች] እንደ ማረሻና ማጭድ የመሳሰሉትን የእርሻ መሣሪያዎች የሚሠሩ ናቸው። እኛ አባቶቻችን ሲሞቱ እንደምናደርገው ሁሉ አንጥረኛ አባቱ ሲሞት ልጅ ተተክቶ የአባቱን

ስራ ይሰራል። የአንጥረኛውን መሬት በሐምሌ እናርሳለን፤ በነሐሴ ዘርተን እናርምለታለን፤ በመስከረምና ጥቅምት እህሉን ሰብስበን እናስገባለታለን። እነርሱ ደግሞ የእርሻ መሣሪያዎችን አመቱን በሞላ ይሰሩልናል። እኛም ሆነ ሽማግሌዎች ወደ እነርሱ የምንሄደው አብረን በማደጋችን ነው። ነገር ግን ቡዳው ከሺህ አንድ ሰው እንደ አጋጣሚ ኮከቡ ገጥሞ ደሙ የጣፈጠው እንደሆነ ይበላዋል። ወደ አንጥረኛ መኖሪያ ከሚሄዱት ብዙ ሰዎች መካከል ሊታመም የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ሊሆን ይችላል። ሌሎች በሰላም ሊመለሱ ይችላሉ።

<<ከአንተ በላይ ሕጉ አለ>>

በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ሲጣሉ ወደ ቀበሌ በመሄድ ልዩነቶቻቸውን ይፈታሉ፤ አሁን በሕጉ መገዛት አለባቸው።

[ድሮ] ኃይል ይጠቀሙ ነበር፤ እንቶኔ በጣም ጉበዝ ፤ ደፋር በመሆኑ አንድም ሽፍታ በበሩ ዝር አይልም ይባል ነበር። አሁን ግን የሕግ የበላይነት ስላለ ስለ ድፍረትም ሆነ ፍራቻ የሚያወራ የለም።

በላቸው (ወንድ፤ እድሜ 68) ፤ አንጥረኛ ኢ.ትዮ.18

በድሮ ጊዜ ሀብታም እኛ ነበርን። ሰው ይበላሉ እያሉ ስማችንን ያጠፉት እነዚያ መሃይም ሰዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያናትን የምናንፅ፤ መኖሪያ ቤቶችን የም ንጠግን እኛ የእጅ ሙያተኞችና ሠራተኞች ሆነን እያለን ጋብቻ ከእነርሱ ጋር እንዳናደርግ ይከለክሉናል። ይህን ስሜታቸውን አሁንም አልተውም። አሁንም እንኳ እነዚህ የሚያማምሩ ቤቶች በእኛ መሠራታቸውን እያወቁ በሚያዩን ጊዜ ፊታቸውን ያዞራሉ። ሕፃን ልጅ ከያዙ እንዳናየው ይሸፍኑታል። ሚስቴ ጠላ ሻጭ ከሆነችም አንድ ገበሬ ከእርሷ ከሚጠጣ ራቅ ያለ ቦታ ሄዶ ከሌላ ቤት ቢጠጣ ይመርጣል። በእኛ ላይ ምንም ጥፋት አላዩም፤ ግን የተለመደ የቆየ ባህል በመሆኑ ብቻ ነው። ልክ በቤታችን ጅብ እንደታሠረ አድርገው ያዩታል።

ቢሆንም ካለፈው ጋር ሲነፃፀር እየተሻሻለ መጥቷል ለማለት ይቻላል። ሰዎች እያወቁ በመጡ ቁጥር ይህ ኋላቀርና የድንቁርና አስተሳሰብ ይለወጣል ብለን እናምናለን። በኑሯችን እኛ የተሻልን ሆነን በማየታቸው ቅናት አለባቸው። አንድ መርፌ እንኳ መሥራት አይችሉም። ገበሬዎች ያለ እኛ መኖር አይችሉም።

አሁን እኩልነት አለ። እኔ ቁመቴ አጭር ፣ [ከድሃ] ቤተሰብ የተወለድኩ ብሆንም አንድ ታዋቂ ትልቅ ሰው ቢመጣ ፣ ያሻኝን ገላምጬ ብናገረው እኩልነት ስላለ ምንም አልሆንም።

በድሮ ጊዜ ሕሊናው ስለሚከለክለው ትንሹ ትልቁን አይሰድበውም። አባቶቻችን ሲነግሩን ሽማግሌዎች ሲመጡ ታናናሾች ከመቀመጫቸው ተነስተው ያስቀምጧቸው ነበር። አሁን ግን እኔም ጭምር አንድ ጊዜ ከተቀመጥኩ አልነሳም።

## የጾታ ሚና

ወንዶች ቁጥቋጦችን ይመነጥራሉ፣ ማሳውን ያርሳሉ፣ ያርማሉ፣ ሰብል ይሰበስባሉ፣ ይወቃሉ፣ ሽማም ይሰራሉ፣ በተጨማሪ ሣር አጭደው እንጨት ቆርጠው ቤት ይሰራሉ። ሴቶች በበኩላቸው ውሃ ይቀዳሉ፣ ሊጥ አቡክተው እንጀራ ይጋግራሉ ፣ ወጥ ይሰራሉ፣ እህል ይፈጫሉ። እንዲሁም በአረምና በመኸር ጊዜ ወንዶችን ይረዳሉ። አውድማውን [እበት በመለቅለቅ] ያስተካክላሉ።

በአሁኑ ጊዜ ያሉ ሴቶች ብዙዎቹ ከቀደምቶቹ የተሻለ እረፍት አግኝተዋል። ይሁን እንጂ ገንዘብና እህል የሌላቸው ግን እረፍት የላቸውም። እህል ከሌለህ ልትፈጭም አትችል፣ ወደ እህል ወፍጮም አትወስድ፣ ነገር ግን ገንዘብ ካለህ እህሉን ወደ ወፍጮ መላክ ትችላለህ።



<<ሴቷ: ውሀ ትቀዳለች፤ ሊጥ ታቦካለች፤ እንጀራ ትጋግራለች፤ እህል ትፈጫለች>>

ስሜን መጻፍ ባለመቻሌ በጣም ይቆጨኛል። ብማር ኖሮ ማንም ሰው ጉጅም ይሁን ጠቃሚ ነገር ጽፎ ሲሰጠኝ ይዘቱን ሳላይ አልቀበልም ነበር። አሁን ግን የቀበሌው ሊቀ መንበር ጉጂ ነገሮችንም ቢሆን ጽፎ ቢሰጠኝ ተቀብዬ አሰራጫቸዋለሁ። ልጆቼን ግን እንደ እኔ መሀይም እንዲሆኑ ስለማልፈልግ ቁራን እንዲማሩ ትምህርት ቤት አስገብቻቸዋለሁ። [ዘመናዊ ትምህርት] ከተማሩም በመንግስት ተቀጥረው ይሠራሉ። ለቀበሌም ያገለግላሉ። ካልተማሩ ግን እንኳንስ መንግስት ቀበሌም አይፈልጋቸው።

ምን እየተካሄደ እንደሆነ መስማት እንፈልጋለን።

<u>መገለል</u>

እየጐዳን ያለው አዳዲስ ሁኔታዎችን ማንበብ ወይም መስማት አለመቻላችን ነው… [ዜናን] በቀጥታ ከምንጩ አናገኝም። አንድ ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ የሚያልፍ ሰው ካልነገረን በስተቀር ዜና አንሰማም። እንዴትስ ለመስማት እንችላለን ? ሬዲዮና ስልክ ሳይኖረን? መንግስት ግብር እንድንከፍል ሲጠይቀን የተባልነውን እንከፍላለን። ስለ መኪና አደጋም ሆነ ስለማናቸውም ነገር አንሰማም። ይህን የምንሰማው ወደ ከተሞች ስንሄድ ብቻ ነው።

ማንኛውንም ነገር ለመስማት እንፈልጋለን። ስለ መንግስት ለውጥ፣ምን እየተካሄደ እንደሆነ ሌላ የመሬት መከፋፈል [ አዘማማሚያ] እንዳለ ፣ ስለ ተባይ ማጥፊያዎች ፣ ስለ መንግስት እቅድ ማወቅ እንፈልጋለን። ስለነዚህ ነገሮች አንዱ በእግሩ ተጉዞ መጥቶ ካልነገረን በስተቀር ለማወቅ አንችልም። የንፁህ መጠጥ ውሃ ችግር ስላለብን በከተሞችም ስላለው የቧንቧ ውሃ ለማወቅ እንፈልጋለን።

<u>ማሪዮ</u> ኢትዮ.21

ማሪዮ፤ ዕድሜው 40 ዓመት ፤ ሥራ አጥ ሲሆን የፍለቂት ነዋሪ ነው።

በመማሩ ደስተኛ ነው፤ አንድ ቀን ስራ እንደሚያገኝ ይተማመናል። ምንም እንኳ የመሬት ላራሹ ለውጥ የቤተሰብ ትስስርን ያላላ ቢሆንም የተደረጉት ለውጦች ብዙ ጠቀሜታ እንዳላቸው ያምናል።

በኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት መሬት በጥቂት ባለሃብቶች እጅ ብቻ ነበር። ጢሰኞች/ገባሮች ካመረቱት አንድ አምስተኛውን ብቻ በመውሰድ ቀሪውን ለመሬት ከበርቴው ይሰጡ ነበር። ከዚያም ህዝባዊ አመጽ ተነስቶ እነዚህን ሰዎች ከስልጣን በማስወገድ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ተቋቋመ። በጦርነቱ ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ግቡን ሊመታ ባይችልም ጭሰኝነትን የሚያስወግድ የመሬት ይዞታ ለውጥ ተደረገ። ከዚያም የመሬት ክፍፍል ተደርጐ ብዙ ገበሬዎች ከባላባቱ ጫና በመላቀቅ ነፃ ሊሆኑ ችለዋል።

ትምህርት በእርሻ ላይ ገንቢ ውጤት ያለው እየሆነ ነው።

በዚያን ጊዜ እኔ አድጌ ትልቅ ነበርኩ...[እናም በዚያን ዘመን] እህሉ በተባይ ሲጠቃ አውቅ ነበር። በዚያን ጊዜ በወረዳችን... የነበሩት የግብርና ሚኒስቴር ሰራተኞች ብቻ በመሆናቸው ተባዩን በተለይም በቆላማ አካባቢዎች ለመቆጣጠር አልቻሉም ነበር። የከብት ሀኪሞችም ቢሆኑ ጥቂቶች ስለነበሩ ከብቶቻችንን ለማከም ይቸገሩ ነበር። ይህም ሆኖ ማዳበሪያ ይሰጥ ነበር፤ ገበሬዎች ግን አጠቃቀሙን ስለማያውቁበት ከቤታቸው ወለል ላይ እንደ ማጣበቂያ እያደረጉ ያባክኑት ነበር።

አሁን ግን አልማ (የአማራ ልማት ማኅበር) ወኪሎች ለገበሬዎች ሥልጠና እየሰጡ በአስተራረስ ዘዴዎች ላይ አዎንታዊ ውጤቶችን አስገኝተዋል። የኤስ.ኦ.ኤስ የመስክ ሰራተኞችም በየቦታው ተመድበው ለገበሬዎች ስልጠና እየሰጡ ናቸው። ምንም እንኳ በገንዘባቸው የሚገዙ ቢሆንም ገበሬዎች ማዳበሪያ ለማሳዎቻቸው ለመግዛት በሰልፍ ሆነው ወረፋ ይጠባበቃሉ። በወረዳችን ቀደም ሲል አስራ ሰባት ትምህርት ቤቶች ፤ ሁለት

ወይንም ሦስት የጤና ኬላዎች ነበሩ። አሁን ግን ሃያ አንድ ትምህርት ቤቶች፣ ብዛት ያላቸው የጤና አገልግሎት መስጫዎች ተሠርተዋል። ኤስ.ኦ.ኤስም ገበሬዎችን በተሻሻሉ የከብት ርባታ ዘዴዎች፣ በብድርና ቁጠባ ማኅበራት ተደራጅተው እንዲጠቀሙ በማስተዋወቅ ላይ ነው።

## የቤተሰብ ታሪክ ፣ የቤተሰብ ትስስር

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የኀብረተሰቡ ኑሮ በመሬት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የመሬቱ ባለቤትነት የቤተሰቡን ግንኙነት ጥብቅ አድርጐ እንዳቆየ ይታወቃል። በምሽት አባቶች ከልጆቻቸው ጋር ተቀምጠው አክስቶቻቸውና አጐቶቻቸው እነማን እንደሆኑ ማን የማን ዘር እንደሆነ ይነግሯቸው ነበር።

አሁን ግን መሬት ስለተከፋፈለ እና መሬትን ከዘመድ መውረስ ጥያቄ ስለቀረ የዘር ግንድ እየቆጠሩ ማውራቱ ቀርቷል። ስለሆነም አባቶች የልጆቻቸውን ኑሮ ለማሻሻል መጣር እንጂ የቤተሰብን ግንኙነት ለመጠበቅ እና ለማጠናከር የሚያደርጉት ትኩረት ያነሰ ነው።

## እየተለወጠ የመጣ ማኅበራዊ ግንኙነት

በድሮ ጊዜ የእጅ ሙያተኞች ክብር አይሠጣቸውም ነበር፣ መሬትም አይኖራቸውም። በሽመና ስራ እየተዳደሩ ለባለፀጐች ልብስ ይሰሩ የነበሩት እስላሞችም እንደዚሁ ነበሩ። እስላምና ክርስቲያን

በበጐ አይን አይተያዩም ነበር። የመገናኛ አውታሮች መዘርጋት፤ በወረዳው የመንገዶች መሰራት፤ የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን አሻሽሎታል። በአሁኑ ጊዜ አንተ እስላም ብሎ የሚሳደብ የለም። የእስላም ካድሬዎችም አሉ። ኤስ ኦ ኤስም አንጥረኞች ለህብረተሰቡ የተሻለ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ቢሮና የመሰብሰቢያ አዳራሽ ስለሰራላቸው፤ ይህ ደግሞ የእነርሱ ስራ ምን ያህል ክብር ያለው መሆኑን ህብረተሰቡ እንዲገነዘብ አስችሎታል...

> በአሁኑ ጊዜ ሴቶች በማዕድ ቤት የተወሰኑ አይደሉም።

በመሬት ድንበር፤ በግጦሽ መሬት፤ ከሴት ጋር በሚደረጉ ያልተፈቀዱ ግንኙነቶች፤ ግጭቶች እየተፈጠሩ አሰቃቂ የሆኑ የአካል ጉዳቶችና... ግድያም ጭምር እያስከተሉ ናቸው። በተለይ በቆላው አካባቢ ወንጀል አልቀነሰም...

ሴቶች እንደ ድሮው በማዕድ ቤት ተወስነው አልቀሩም። በአካባቢው ስብሰባዎች ሲደረጉና የልማት ስራዎች ሲከናወኑ ፤ በኤስ ኦ ኤስ ስልጠናዎች ሲሰጡ በእኩልነት ይሳተፋሉ። ወንዶችም በእነዚህ ከቤት ውጭ በሚካሄዱ ክንውኖች ሴቶች ሲሳተፉ አይነቅፏቸውም።

በእኔ እድሜ እንኳ ቅምጥ ማስቀመጥ በሚስቶች የተፈቀደ እንደነበረ አውቃለሁ። ባልየው ለአቤቱታ ወይም ለሌላ ጉዳይ ወደ ወረዳ ሲሄድ ለሚስቱ ከቅምጡ ጋር እንደሚያድር ሲገልጽላት ምንም ሳትል ሃሣቡን ተቀብላ ከሌላ ሰው ቤት ከሚሄድ ከእርሷ ጋር መሄዱ የተሻለ ነው ትላለች። ሰውየውም ቅምጡን እንደ አንድ ቤተሰብ አባል በመቁጠር ለእርሷም ሆነ ለልጆቿ የሚማሩበት ድጋፍ ይሰጣል። ወንዶች ከአንድ ፍቅረኛ ጋር ስለማይዕኑ ፤ ከአንድ ቤት

ወደ ሌላው በመሄድ ኤድስ በተባለው በሽታ ይለከፋሉ፣ ፍቅራቸውም ለብዙ ጊዜ የሚቆይ አይደለም።

## ኃላፊነት

እንደማስታውሰው የቅርብ ዘመድ፣ ልጆች ወይም ደጋፊ የሌላቸው አቅመ ደካማ እና አረጋውያን ወደ ሰው ቤት ከመጡ ባለቤቱ እያበላ ፣ እያጠጣ ፣ መኝታ በመስጠት ካቆያቸው በኋላ ወደ ጎረቤት እንዲተላለፉ በማድረግ ህብረተሰቡ እንዲንከባከባቸው ይደረግ ነበር፣ እነዚህ ሰዎች እልፍ በመባል ይጠራሉ። በአሁኑ ጊዜ ግን እነዚህ አዛውንቶች በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢና በመስጊድ አካባቢ በእርዳታ ማከፋፈያ ማዕከሎች የምግብ እርዳታ ለማግኘት ተኮልኩለው ይታያሉ። አብዛኞዎቹ ሰዎች በበሽታ ዘመዶቻቸውን ያጡ ከቆላ አካባቢ የመጡ ናቸው። መንግስት አልፎ አልፎ እርዳታ ቢሰጣቸውም በቂ ስላልሆነ አንዳንዶቹ ወደ ከተማ እየገቡ ናቸው። እዚህ ያለው ሕዝብ ደሃ ስለሆነ ድጋፍ ሊሰጣቸው አልቻለም።

## የመቄት ወግና ባህርይ

ቆለኞችና ደገኞች በወግና በአለባበስ ዘይቤአቸው እንኳን ይለያያሉ። በደጋ የሚኖሩ ወንድ ወጣቶች ሱሪ፣ ጋቢ፣ ጫማና፣ ጥምጣም ሲያደርጉ ሴቶቹ ደግሞ በተለይ በበአላት ቀን ከጥጥ የተሰሩ በጥበብ ያጌጡ ቀሚሶችንና ረጃጅም ልብሶችን ይለብሳሉ።

| |
|---|
| እትዬ (ሴት፣ 58 ዓመት) ፣ የልምድ አዋላጅ ኢትዮ.14<br>ስለአባቶቹ፣ ስለአያቶቹና ስለቅድመአያቶቹ እኔ ካልነገርኩት ልጁ በቀላሉ በሌሎች ሰዎች ሊጠቃና ሠለባ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የዘር ሃረጉን (ወገኑን) ካወቀ የእነርሱን ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል። |

የቆላ ወጣቶች ግን ከደገኞች በተለየ መልኩ በአብዛኛው ቁምጣዎችን ይታጠቃሉ። ሴቶቹ ደግሞ ፀጉራቸውን አሳድገው ቅቤ ይቀባሉ። ከሙቀቱ የተነሳ የሚለብሱት ልብስ ቀለል ያለ ነው። በደጋ የሚኖሩ አዛውንቶች ጋቢ ለብሰው፣ ጭራ፣ ዱላ ይዘው ሲታዩ እስላሞቹ ደግሞ ባለጀንፎ በትር ይይዛሉ።

አስደሳች ባህላዊ
ጨዋታዎች
ቀጣይነት
እንዲኖራቸው
እፈልጋለሁ።

በባህርይ በኩልም ቀለኞችና ደገኞች ይለያያሉ። ቀለኞች ትጥቃቸው የተሻሻለ ፣ በትራቸው እንኳ ሳይቀር ጠንከር ያለ ሆኖ በቀላሉ የሚናደዱና ጥል የሚያነሱ ናቸው።

በነሐሴ ወር ውስጥ በአንድ ሰፈር የሚኖሩ ወጣት ወንዶች ጥንካሬያቸውን ለማወቅ የሚያስችላቸው ከአቻ ጓደኞቻቸው ጋር የጅራፍ ግርፊያ ያደርጋሉ። የዚህ አይነቱ ልምድ የሚቀጥል አይመስለኝም ፣ ምክንያቱም አንዳንድ ወጣቶች አይናቸው ሲጠፋ አንዳንዶቹ ደግሞ ግርፊያው ሲጠነክርባቸው ወደ ሰው ቤት ተንደርድረው በመግባት እቃዎችን በመሰባበርና ሽማግሌዎችን ገፍትረው ወደ ጉድጓድ በመጣል ሲሸሹ አይቻለሁና። በገና እና በአንዳንድ በአላት የፈረስ ግልቢያ እሽቅድድም ውድድሮች ይደረጋሉ። እነዚህ በቆላው አካባቢ የተለመዱ አይደሉም።

ብርሃኑ (ወንድ ፣ 70 ዓመት) ኢ.ትዮ. 5

ተኩላ እና ሚዳቋ ስታይ ለመያዝ እንደምትሽቀዳደም ሁሉ ሚዳቋም ደግሞ ለማምለጥ ትፈተልካለች። በአሁኑ ጊዜ የደገኞችና የቆለኞች ሁኔታ እንደዚሁ ነው። ደገኞች ቆለኞችን በሚመለከት ሕግ አላቸው፣ ቆለኞችም እንደዚሁ፣ እርስ በርሳቸው መጣላት ነው።

በ1946 የራሴ ሬዲዮ ነበረኝ። አሁን ደግሞ ልጆቻችን የራሳቸው ሬዲዮ ገዝተዋል። ስችል ወደ እነርሱ እየሄድኩ አዳምጣለሁ። በመኪናና በአየር መጓጓዙ፣ ከዚህ ተቀምጦ ርቀት ከሚኖረው ሰው ጋር በስልክ መነጋገሩና በሌላው ዓለም ካለው መንግስት ጋር በየቀኑ ግንኙነት ማድረግ መቻሉ፣ እነዚህ ሁሉ የሳይንስ ግኝቶች ያስደንቁኛል።

የፈረስ እሽቅድድም፣ የገና ጨዋታ ውድድርና በጥምቀት በዓል በየቤተ ክርስቲያኑ በመሄድ ሴቶችና ወጣቶች የሚዘፍኗቸውን ዘፈኖችና ጭፈራዎችን እወዳቸዋለሁ። ባህላዊ ዘፈኖችንና ጭፈራዎችን እወዳለሁ። በቀብር ጊዜ በፈረስ ሆነው የሞተውን ሰው በማድነቅ ሌላውን በማናናቅ የሚደረድሩትን የሙሾ ግጥሞች አልደግፍም። አስደሳች የሆኑት ባህላዊ እሴቶች እንዲቀጥሉ እፈልጋለሁ።

## የውጭ ዜና

ሬዲዮ ስላለኝ እያዳመጥኩ በሃገር ውስጥ ስላሉ ክንውኖችና ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታዎችን አውቃለሁ። የወረዳውና የቀበሌው አስተዳደርም ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ አባላት ግንኙነት እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል።

## ረሀብን ስለመቋቋም

በ1973 ከባድ ረሃብ ገብቶ ነበር። ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ እኔ ሕፃን ብሆንም ሰዎች ወደ ወረዳ ፣ አውራጃና ወደ ክፍለ ሃገሩ ባለሥልጣኖች እየሄዱ መንግስት የምግብ እርዳታ እንዲያደርግላቸው ይጠይቁ ነበር። የክፍለ ሃገሩ ባለሥልጣናትም ዳቦና ገንዘብ ሰጥተዋቸው ነበር። በ1984 እንደዚሁ ሌላ ከባድ ረሃብ ስለገባ ሰዎች ከዚህም ከሌላም ወረዳ የሚኖሩ

> መሬት፡ ሳይቋረጥ ይታረሳል፣ጦም አድሮ አያውቅም

ከብቶቻቸውን በመሸጥ ቀሪዎቹን በማረድ በሏቸው። ረሃብን ለመቋቋም ውሽእሽ የሚባል ስር እየቆፈሩ ይበሉ ነበር። በተለይ በቆላ የሚኖሩ ሰዎች ከእጃቸው የገባውን እህል ጥሬውን ሳያበስሉ ይመገቡ ነበር። በዚህን ጊዜ መንግስት ችግሩን ለማቃለል የሰፈራ መርሃ ግብር ቀይሶ ሰዎችን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ወሰዳቸው። አንዳንዶቹ ከአዲሱ አካባቢ አገር ለመለማመድ ባለመቻላቸው ሲያልቁ ሌሎች ደግሞ በበሽታ ሞተዋል።

<u>መሳይ</u> ኢትዮ.13

መሳይ እድሜው 28 ሲሆን ደንቀና ያለው ደብር ኰሚቴ ኃላፊ ነው። እንደሌሎቹ ሁሉ ለተሻለ ትምህርት ዕድል ቢያገኝ ይወድ ነበር። በደርግ ጊዜ ወደ ሰፈራ ሄደው የነበሩት ሰዎች ተመልሰው ወደ ጥንት ቀያቸው በመምጣት በአካባቢው (የተፈጥሮ) ሀብት ላይ ጫና ፈጥረዋል።

በእኔ ትውልድ ቦታ ኑሮ እያደር እየተባባሰ በመሄድ ላይ ነው። ለዚህም ምክንያቱ የአፈሩ በጐርፍ መሸርሸርና በነፋስ መወሰድ ሲሆን የመሬቱ ምርታማነት ከአመት አመት እየቀነሰ ነው። ድርቅም ሁኔታውን እያባባሰው ስለሄደ ኅብረተሰቡን ለችግር ሊያጋልጠው ችሏል። መሬቱ ሳያቋርጥ ይታረሳል እንጂ አያርፍም። ገበሬዎችም ክትርና እርከን ስለማይጠቀሙ መሬቱ በጐርፍና በነፋስ ይጠቃል። በዚህም ምክንያት ምርት ይቀንሳል...

ድሮ የመሬት እጥረት ስላልነበር ከፊሉ መሬት ሳይታረስ ተትቶ ከፊሉ ይታረስ ነበር። ያልታረሰው መሬት አመት አርፎ

ሲታረስ ምርታማ ይሆናል። አሁን ግን የማይታረስ መሬት ስለሌለ መሬቱ ለስልሶ ፤ ለሸርሸራ ተጋልጦ ምርታማነቱ ቀንሷል። የህዝብ ብዛት እየጨመረ፤ መሬቱ እየተበጣጠሰና እያነሰ ስለሄደ ኅብረተሰቡን ለችግር አጋልጦታል። ቀደም ሲል ደርግ አንዳንድ ገበሬዎችን ወደ ሰፈራ በመውሰድ ከለም መሬቶች በማስፈር ያለውን መጨናነቅ እንዲቀንስ ቢያደርግም ሰፋሪዎቹ ተመልሰው ወደ ቀያቸው በመምጣታቸው የመሬቱን እጥረት አባብሰውታል።

## ለተሻለ ሁኔታ (ኑሮ) ትንሽ ለውጥ

ገበያ እዚህ እና ትንሽ እራቅ ብሎም አለ። እነዚህ ገበያዎች የጥንት ቢሆኑም በቅርብ እየተስፋፉ ስለመጡ ለሸማቾች አስፈላጊ እቃዎችን እያመጡላቸው ነው። በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ጠንክረው በመስራት ተፈላጊ ዕቃዎችን ለደንበኞቻቸው እያቀረቡ ናቸው...



<<መሬት የሌላቸው ነጋዴዎች እየሆኑ ነው>>



አካባቢ

በዚህ አካባቢ ጫካ አልነበረም። በ1995 ኤስ.ኦ.ኤስ መጥቶ ወንድ ሴት ሳይለይ በልማት እንዲሳተፉ በማስተባበር ፣ ችግኝ እንዲተክሉ ፣ የተለያዩ የሳር አይነቶችን እንዲዘሩ፣ እርከኖችና ክትሮች እንዲገነቡ፣ ችግኞችን ለደን ልማት እንዲያዘጋጁ አድርጓል። ዛፎቹ ሲያድጉ መሬቱን ከአፈር እጥበት ከመከላከላቸውም በላይ ዝናብ እንዲመጣ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ አመዳዩና ቅዝቃዜው የዛፎቹን እድገት እየቀነሱት ነው....

ባለፉት ጥቂት አመታት እኔ እራሴ ሳልቀር ብዙ ለውጦችን አይቻለሁ። ለምሳሌ አምናና ካቻምና በበልግ ሳይቀር በቂ ዝናብ ስለጣለ በሰኔ ጥሩ ምርት አግኝተናል። ዛሬ ግን በግንቦትም ዝናብ የለም። ስለሆነም የአየር ለውጥ በመኖሩ የምናገኘው የዝናብ መጠን የተዛባ ነው። ገበሬዎች መሬታቸውን አርሰውና መሬቱን አለስልሰው ዝናብ ሲጥል ለመዝራት ዝግጁ መሆን አለባቸው። ትንሽ ዝናብ እንኳ ቢኖር እህሉ በቀላሉ ሊያድግ እንዲችል ማዳበሪያ ቢጠቀሙ የተሻለ ነው። ስለሆነም ጥሩ ውጤት ለማግኘት የተሻሉ የእርሻ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል።

<u>የካባ (ሴት ፣ 25 ዓመት)</u> ኢትዮ.8

በአሁኑ ጊዜ የፈለግኩትን መሸጥ እችላለሁ። በሬ ካለኝ ሸጬ ብፈልግ ላም ወይም በግ ወይንም ፍየል ገዝቼ በማርባት ለመጠቀም እችላለሁ። ድሮ ቅቤ፣ ከብት፣ እህል ሸጠህ የፈለከውን ነገር መግዛት አትችልም ነበር። አሁን ግን ነገሮች ስለተሻሻሉ እንቁላል ወይም ዶሮ መሸጥ ትችላለች...

ገበያ እዚህ ብናቋቁም ጠቃሚ ነው። ቀደም ሲል አቋቁመን ነበር። ሰው ግን መምጣቱን አቆመ። እዚህ ገበያ ቢቋቋም ደንበኞች በማግኘት ጠላና ዕቃዎችን ለመሸጥ ከመቻሉም በላይ አካባቢያችን ወደ ከተማ ሊለወጥ ይችላል....... [እኔ] የቆርቆሮ ቤት ሠርቻለሁ። ከተማው ቢያድግ ገበያ ይቋቋማል እኔም ሱቅ ከፍቼ ነጋዴ እሆናለሁ።

## ማኅበራዊ ኃላፊነት

ቅሬ፤ ሰንበቴና ማኅበር አለን። [የቅሬ ጥቅም?] ሰዎች ብዙ ወይንም ጥቂት ዘመዶች ኖሯቸውም አልኖራቸው ቅሬ ሰዎችን እንደወንድም በአንድ ላይ በማስተባበር እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። በቅሬ አማካኝነት ሰው ሲሞት ድሀ ሀብታም ሳይለይ በመተባበር የቀብሩን ስነ ሥርዓት ይፈጽማል። አንድ ሰው በቀብሩ ስነ ሥርዓት ካልተገኘ ይቀጣል። የቅጣቱ መጠን ደግሞ እንደ ጥፋቱ ክብደት ይለያያል።

ቅሬ ሰዎችን እንደ ወንድም አንድ ላይ እንዲሰበሰቡ አድርጓቸዋል።

ሰው ሞቶ ወደ ቀብር ቦታ ሳይሄድ ከቤቱ የተቀመጠ ይህ ከፍተኛ ጥፋት ስለሆነ ቅጣቱ ይከብዳል። አስክሬን ካልተሸከመ ፤ ቀሪ ከሆነ ደግሞ ወቀሳ ይደርስበታል። ጥፋቱንም በማመን የሚጥሉበትን ቅጣት ይቀበላል። እምቢ ካለ ግን ከቅሬው ይባረራል። እኔም የአንድ ዱብር ኃላፊ ነኝ፤ የተጣሉትን አስታርቃለሁ፤ አስማማቸዋለሁ፤ እንደዚህ ያሉ አባላትን እመክራቸዋለሁ....

ከእነርሱ ጋር ከመጣላት ሌሎችን ማስተማር ይሻላ።

አይነ ስውራንና ደንቆሮ የሆኑ ሰዎች ልጆች ካሏቸው ይንከባከቧቸዋል። አይናቸውን ሲጋርዳቸው ወደ ሆስፒታል በመውሰድ ያሳክሟቸዋል። በሕክምና ሊድኑ ካልቻሉም እስኪሞቱ ድረስ እንክብካቤ በማድረግ ይጦሯቸዋል። መሬት ኖሯቸው [ልጅ የሌላቸው] ከሆኑ ደግሞ አንድ እንደ ልጅ በመቅረብ መሬቱን እየተጠቀመ እስኪሞቱ እንዲጦራቸው ከዚያም መሬቱን እንዲወርስ ያደርጋሉ።

## የመቄት ማንነት መለያ


የመቄት ወረዳ ነዋሪዎችን ከሌሎች የሚለዩን ብዙ ባህሪያት አሉ። በአነጋገራችን፣ በአመጋገባችን እንዲሁም በአለባበሳችን እንለያለን። እንዲሁም መቄት ነዋሪ በመሆን ብቻ አንድ አይነት ዘዬ ፣ አመጋገብ፣ ወግ፣ አካሄድ፣ ይኖረዋል ማለትም አይደል። ልዩነቶች አሉ፣ ለምሣሌ ደገኛውንና ቆለኛውን የፊቱን ገጽታ ብቻ በማየት ለመለየት ትችላለህ። ቆላው ጤፍ፣ አጃ፣ ስንዴ፣ እንደ አተርና ባቄላ ያሉትን ጥራጥሬዎች ሲያበቅል ደጋው የሚያበቅለው ገብስ ብቻ ነው።

እኛ ትልቅ አክብሮት ያለን ለሃይማኖታችን ነው። ሀይማኖታችን በሌሎች እንዲበረዝ አንፈልግም።

## <<ትምህርት ነገሮችን በትዕግስት እንድትቀበል ያደርጋል>>

ወላጆቼ ትምህርት ቤት ቢያስገቡኝም ትምህርቴን ሳልጨርስ አቋረጥኩ። ትምህርቴን [ቀጥዬ] ቢሆን ኖሮ ኑሮዬን በከፍተኛ ደረጃ አሻሽል ነበር። አንድ ሰው ከተማረ ነገሮችን በትዕግስት በመቀበልና ቀዝቀዝ በማለት ፣ ጥሉን በማብረድ፣ ሰዎች በኃይል እንዳይጠቀሙና እንዳይደባደቡ ከማድረጉም ባሻገር ለጥል እንኳ ገፍቶ ቢመጣበት አይደባደብም።

ብርሃኑ (ወንድ፣ 70 ዓመት) ኢትዮ.5
[ስለ አቅመ ደካሞች] ያላቸው አመለካከት የሚያመላክተው እነርሱ አንድ ቀን እንደ አቅመደካሞች እንደማይሆኑ አለማሰባቸውን ነው። ችላ ብለው ትተዋቸው ይሄዳሉ። ፈጣሪያችን አቅመ ደካሞችን እንድንረዳ ያለንን እንድናካፍላቸው ያዘዘን ቢሆንም ሰዎች ግን ዘወር ብለው እንኳ አይመለከቷቸውም። አፍንጫቸውን ተሸፍነው ያልፏቸዋል። በድሮ ጊዜ ሰዎች ማርና ቅቤ ወተትና ስጋ ይመገቡ ስለነበር ብርቱ፡ ነበሩ፣ ፍቅርም ነበር፣ አቅመ ደካሞችም እንደ አሁን አይበዙም ነበር።



የመሬት ገፅታ

ዳላንታ በሚባል ቦታ ትምህርት ቤት ገብቼ ከተማርኩ በኋላ ወደ እስታይሽ ሄጄ እስከ ስድስተኛ ክፍል ተምሬ ከዚያም ወደ ፍልቃት ሄጄ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተማርኩና ወደ ዘጠነኛ ክፍል እንዳለፍኩ በመንግስት ለውጥ ስለመጣ ወላጆቼ እኔን ሊደግፉኝ ስላልቻሉ ትምህርቴን እንዳቋርጥ ተገደድኩ። ከዚህ አካባቢ ማንም ሁለተኛ ደረጃን ያጠናቀቀ የለም። አንድ የማውቀው ቢኖር ስምንተኛ ክፍልን አጠናቅቆ በወረዳው አስተዳደር ሠራተኛ የሆነውን ነው።

ትምህርት እውቀትን እንድትገበይና ኑሮህን እንድታሻሽል ይረዳሃል፣ እንዲሁም ብዙ እንዳትከራከርና እንዳትናገር ፣ ከሰው ጋር ለመጣላት እንዳትቸኩል ይረዳሃል። ብዙም እንድታውቅ ጉጉት ይፈጥርብሃል። ስለሆነም ሰዎች እንዲማሩ አዘውትሬ እመክራለሁ።

በድሮ ጊዜ ሴቶች ኋላ ቀር ስለነበሩ ወንዶች የቤተሰብ ኃላፊዎች ሆነው ያስተዳድሩአቸው ነበር። አሁን ግን ሴቶችም ፣ ወንዶችም ንቃት ስላላቸው ሁለቱም በጋራ ሆነው ኑሮአቸውን ለማሻነፍ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። እርስ በእርስ እየተመካከሩ በመወሰን ቤተሰቡን ይመራሉ። በአሁኑ ጊዜ ሴቶች የቤተሰብ ኃላፊ እየሆኑ ናቸው።

## ድርቅና ሰፈራ

እኔ ልጅ እያለሁ ድርቅ ገብቶ እንደነበረ እሰማ ነበር፣ ይሁን እንጂ መቼ እንደነበር ጠይቄ አላውቅም። የእንስሳት ቆዳ እየቀቀሉ ፣ እንሰሳት የሚመገቡትን ማገጥ የተባለውን ሳር ይበሉ እንደነበር ይነገራል። እኔ በአይኔ አላየሁም የሰማሁት ግን ይህን ነበር። በ1984 ብዙ የሰው ሕይወትና እንሰሳትን የጨረሰ አሰቃቂ ድርቅ ገብቶ ነበር።



የመሬት ገፅታ 2

በዚህም የተነሳ ደርግ ብዙ ሰዎችን ወደ ባሌና መተከል ወስዶ አስፍሯል። ድርቅ በየአመቱ የሚከሰት ችግር እንደመሆኑ አዲስ ነገር አይደለም። ይሁን እንጂ ገበሬዎቹ ይህን ነገር ስለማያጤኑት ተጠቂዎች ይሆናሉ።

[በ1984] እኔ ተማሪ ስለነበርኩ የምተዳደረው በቤተሰቦቼ ነበር። ችግሩን ልንቋቋመው የቻልነው ከብቶችን በመሸጥ እህል በመሸመት ነው። በ1985-86 ግን ጥሩ ምርት አገኘን። ምግብም ሆነ መጠለያ በነፃ ይገኝ ነበር። ሰውነታቸው ጠንከር ያለው ለጊዜው በመጠለያዎች ከተመገቡ በኋላ ወደ ስፈራ ሲወሰዱ አቅመ ደካሞች ደግሞ በየመጠለያው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይመገቡ ነበር።

አባቶቻችን [የምግብ እጦት ችግር] አላጋጠማቸውም። እኛ ግን አሁን ያለንን ገቢ አውቀን በበጀት መጠቀም መልመድ አለብን። አንዳንድ የተማሩ ሰዎች እንደሚነግሩን ለነዳጅ፤ ለሌሎች አስፈላጊ ወጭዎች ብለው ገንዘባቸውን በቁጠባ በመያዝ ይህን ᾿ያህል ለዚህ ወር፤ ለሚቀጥለው ደግሞ ይህን ያህል ብለው በአቅማቸው በመመደብ ለመጠቀም መወሰን ይኖርባቸዋል። አንድ ሰው ያለውን ገንዘብ በበጀት መድቦ ለመጠቀም ካልቻለ እንደገና ካጠፋው እንኳንስ ዓመት ሊኖርበት ቀርቶ ለወርም አያደርሰውም።

> ድርቅ ራሱ
> አዲስ ነገር
> አይደለም።

<u>ሙልዬ</u> ኢትዮ 15

ሙልዬ 37 ዓመት እድሜ ያለውና የመቄት ነዋሪ ሲሆን የግብርና ዘዴዎች እየተሻሻሉ መምጣታቸውን፤ ትምህርት በመስፋፋቱ እና ሌሎች የልማት ሥራዎች በጉ ለውጦች ናቸው

የሚል አመለካከት አለው። የቻይና መንገድ መሠራት ልዩ ግምት የሚሰጠውና በመጭዎቹ ሁለት አሥርተ ዓመታት አብዮታዊ ለውጦች እንደሚኖሩ ይገምታል።

ምንም እንኳን ሁሉም ገበሬዎች ባይጠቀሙም አንዳንድ ገበሬዎች ማዳበሪያና ምርጥ ዘር በመጠቀም በኤክስቴንሽን ሰራተኞች በመረዳት ምርታቸውን በእጥፍ አሳድገዋል።

በድሮ ጊዜ እንደ አሁኑ አንድ ቤተሰብ አራት ወይንም አምስት ላሞች ብቻ አልነበሩትም። አቶ እንቶኔ <<ጨጓራ ለበሰ>> ይባል እንደነበር ይናገራሉ። ይህም ማለት ከ50 እስከ 100 የሚደርሱ ጥገት ላሞች ነበሩት ማለት ነው። ይህም የሚያመለክተው ብዙ ከብቶችን ያረባ እንደነበረ ነው። በአሁኑ ጊዜ የሕዝብ ብዛት ስላለ ለመኖሪያም ጭምር ስለሚጠቀምበት በቂ የግጦሽ መሬትና መኖ የለም። ይህም አንዳንድ ሰዎችን ከወፍጮ ቤቶች ፉርሽካ በመሰብሰብ ብቻ ለከብቶች መኖ በመጠቀም በትንሽ ይዞታ ላይ ዘመናዊ የከብት እርባታ ዘዴዎችን በመጠቀም የከብት ዕርባታ ለማካሄድ ገፋፍተዋቸዋል።

## የዘመናዊ ዘዴዎች ጥቅም

ድሮ የህዝብ ቁጥር አነስተኛ፣ የእርሻ መሬቱም ደግሞ በተደጋጋሚ ባለመታረሱ ምርቱ የተሻለ ነበር። አሁን የህዝብ እድገትና የመሬት መጣበብ ማለት መሬትን ደጋግሞ ማረስና ዝቅተኛ የእህል ምርት ውጤት ማለት ነው። ቢሆንም ዛፎችን በመትከል፣ እርከኖችንና ክትሮችን በመገንባት፣ የግብርና ቴክኖሎጂን

በመጠቀም፣ የመሬት መታጠብን በመከላከል፣ ገበሬው ምርቱን ከፍ ሊያደርግ ችሏል።

ድሮ ድሪና ደገዛ የተባሉትን ተባዮች ለማጥፋት በጭራሮ ይከላከሉና ይገድሉ ነበር። ይህ ዘዴ አመቺ ሆኖ ባለመገኘቱ በኤክስቴንሽን ሰራተኞች አማካኝነት የተባይ ማጥፊያ መድሃኒቶችን በመርጨት ነው የሚጠቀመው። የኤክስቴንሽን ሰራተኞችም ገበሬዎች ወንዞችን ገድበው ለመስኖ እንዲያውሉ በማድረግ እንደ ቃሪያ፣ ሽንኩርት ፣ በቆሎ ያሉትን አትክልቶች እንዲያለሙ እያበረታቷቸው ነው።

መሬቱ እየታጠበ፣ ወደ ምድረ በዳነት እየተለወጠ በመሄዱና ብዙ ጅረቶች በመኖራቸው፣ መሬቱን በገመድ በመከፋፈል ሰፊ ቤተሰብን ለማስተዳደር አላስቻለም። ለዚህ አይነተኛ መፍትሔው የቤተሰብ የመሬት ይዞታውን እንዲጨምር ማድረግ ወይም የቤተሰብ ምጣኔን ተጠቅሞ የሕዝብ ብዛትን መቆጣጠር ነው።

ጤና ጣቢያዎችና ትምህርት ቤቶች በየጐጡና በየገበሬ ማኅበራቱ ተገንብተዋል። የከብት ሕክምናም በየጓሮአችን እየተዳረሰ ነው። በኅብረተሰቡ ተሳትፎም መንደሮችን ከዋናው መንገድ ጋር የሚያገናኙ መጋቢ መንገዶች እየተሰሩ ናቸው። እነዚህ ክንውኖች የአካባቢውን የኢኮኖሚ ልማት እያፋጠኑት ነው።

[እነዚህ]... ክንውኖች እመርታ ካሳዩና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቅመን ምርት ማሳደግ ከተቻለ በሚመጡት ሃያ አመታት አብዮታዊ ለውጥ እናያለን።

## ጋብቻና ፍቺ

> አሁን ወጣት ተጋቢዎች እርስ በርሳቸው ይመራረጣሉ።

ድሮ ወላጆች ልጆቻቸው የሚያገቡትን ወስነው ተጋቢዎች እንዳያውቁ በሚስጥር ይዘው ሰርጋቸውን በመደገስ ይድሯቸው ነበር። አሁን ግን ተጋቢዎች እርስ በእርስ ተመራርጠው ከተጫጩ በኋላ ወላጆቻቸው የሰርግ ድግስ እንዲያዘጋጁ ይነግሯቸዋል።

ቀድሞ ጋብቻ በሽማግሌዎች አማካኝነት እንደሚፈፀም ሁሉ የሰማንያ ጋብቻ ፍቺው የሚፋረሰው በባልና ሚስት የጋራ ስምምነት በሽማግሌዎች ወይንም በቤተሰብ ጉባኤ አማካኝነት ነው። ለፍቺ ዋና ምክንያት የሚሆነው አመንዝራነትና ባልየው ከጋብቻ ውጭ ልጅ ሲደቅል ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ አሁንም ባልየው ከቅምጡ የአባላዘር በሽታ በማምጣት ሚስቱን ሲበክል ነው። አንዳንድ ጊዜም ሚስት ከውሽማዋ በሽታውን በማምጣት ባሏን ልትበክል ትችላለች።



<<የከብት ሕክምና አገልግሎትም በየቂያችን መዳረስ ጀምሯል>>



የከብት ዕርባታ 2

## ልጆች ውለታ - የመክፈል - ወይም የአለመክፈል

በድሮ ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ባህላዊ ቄስ ትምህርት ቤት በመላክ ካስተማሩአቸው በኋላ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ካህናት በመሆን ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ። ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ካልተላኩ ደግሞ የአባቶቻቸውን ፈለግ በመከተል ገበሬዎች ይሆናሉ።

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት እያስገቡ በማስተማራቸው ልጆቹ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ሥራ ይዘው የተባረኩት ከማግባታቸው በፊት ወላጆችን እየረዱ ኑሮአቸው እንዲሻሻል ያደርጋሉ። ይህን የሚያደርጉትም እነርሱን በማሳደግና በማስተማር የከፈሉትን መስዋዕትነት ስለሚረዱ ነው።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ልጆች ገቢያቸውን ለልብስ፣ ለጌጣ ጌጥና ለመኪና መግዣ እያዋሉ ምቾት ያለው ኑሮ ይኖራሉ። ወላጆቻቸውንም ለመርዳት አይፈልጉም፣ ወላጆቻቸውንም ይክዳሉ።

በላይ አያል (ወንድ፣ 18 ዓመት) ቄስ ለመሆን በመማር ላይ ያለ ኢትዮ.6
ደገኞች ከቆለኞች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉት ቆለኞች የዕድ ባለሙያ በመሆናቸው ለደገኞች አስፈላጊ የሆኑትን የእርሻ መሣሪያዎች ስለሚሰሩላቸውና ለእርሻ መሬቶችና ለማገዶ እንጨት ሲሉ ነው። የከተማ ሰዎች የገጠሩን ህብረተሰብ በንቀት ይመለከቱታል። ለዚህም ምክንያት የልብሳቸውንና የጤንነታቸውን ሁኔታ በማየት ነው። ሁኔታው ግን ይህ መሆን አልነበረበትም፣ ምክንያቱም የሚበሉትን ምግብ፣ ለልብ የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን ፣ የሚያመርቱት ገበሬዎች በመሆናቸው ነው። አሁን ግ ገበሬዎች ከከተማ ነዋሪዎች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉበት ምክንያት እቃዎችንና ልብሶችን ከከተማ ስለሚያገኙ ነው።

## ማኅበራዊ ግንኙነት

ሰዎች በአንድ አካባቢ አብረው የሚኖሩ፤ የጋራ ቋንቋና ባህል ስላላቸው አንዱ ከአንዱ ላይ መጥፎ ነገር አይፈጽምም፤ እስላሞች በሽመና፤ ክርስቲያኖች በግብርና ፤ አንጥረኞች የግብርና መሣሪያዎችን በመስራት እንዲሁም ክርስቲያኖች ለአንጥረኞች ልጆች የክርስትና አባት በመሆን እየተደጋገፉ ይኖራሉ። ደገኞችና ቆለኞችም መልካም ግንኙነት አላቸው።

የእጅ ሙያተኞችና ገበሬዎች ቅርብ ግንኙነት ስላላቸው በሰርግ፤ በክርስትናና የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን ነዋሪዎች በየአመቱ ቅዱሳንን ሲያከብሩ ተጠራርተው ይገባበዛሉ። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች አንጥረኞች ሌሎች ሰዎችን ይበላሉ ይላሉ። እኔ ግን በምኖርበት አካባቢ ሲበሉ አላየሁም። በነገሩም አላምንበትም። በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ሀይማኖተኛ ፤ ባህላቸውን አክባሪና እርስ በእርስ መልካም ግንኙነት ያላቸው ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች በጥቃቅን ነገሮች ይጣላሉ፤ ለምሣሌ አንድ ሰው የተቀመጠበትን ድንጋይ ቢወስድበት የእኔ ነው በማለት ሊደበድበኝ ወይም ሊገድለኝ ይችላል። ይህም አርቆ አለማየት (አለማስተዋል) ነው።

> በላቸው (ወ፤ 68 አመት እድሜ)አንጥረኛ ኢትዮ 18
> ቃለ መጠይቃችሁን ከጀመራችሁ አንስቶ ብዙ ተወያይተናል። የተማርኩ ቢሆን ኖሮ ፤ መልሶችን ሁሉ እጽፍላችሁ ነበር። አሁን ግን ነገ ብትጠይቁኝ የመለስኳቸውን መልሶች እንኳ አላስታውሳቸውም። ባለመማራችን የሚጐድለን ምን እንደሆነ ታያላችሁ። በአባቶቻችን ጊዜ ትምህርት ቤቶች ስላልነበሩ ጊዜው የመሐይማን ጊዜ ነበር። ልጆችን ለማስተማር ስል 33 አመት በሰው አገር ፤ ጉጃም ኖሬአለሁ። በስራ አለም አንድ ሰው ነጋዴ ለመባል የሚበቃው ማንበብ መፃፍና ቁጥሮችን ማስላት ሲችል ነው።

<<ሴቶች ማንነታቸውን አረጋግጠዋል...>>

በድሮ ጊዜ ሴቶች ከወንዶች ጋር በመሆን የውጭ ወራሪዎችን ለማባረር በተደረገው ጦርነት ስለተፋለሙ እኩል ናቸው ተብሎ ይታሰብ ነበር። አንዳንድ ሰዎች ሴቶችን በአካልም ሆነ በአእምሮ ዝቅተኞች ናቸው ብለው ቢያስቡም ፤ ሴቶች ግን በስራ ውጤታማና በትምህርትም እንደ ወንዶች በመማር እኩልነታቸውን አረጋግጠዋል።

ሴቶች በሳይንስና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆናቸው ፈጣን መሻሻል አሳይተዋል። ሴቶች ራሳቸውን ጠቅመው አገራቸውን ለመርዳት ከቤተሰባቸው ውስጥም ሆነ ውጭ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ።

ትምህርት ተንከባክበህ ለምታሳድጋቸው ልጆችህ ቀርቶ ለማይዛመድህም ቢሆን ጠቃሚ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ ሌሎች የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላትም ትምህርት ማግኘት አለባቸው። ወንዶችና ሴቶች ሲማሩ እኩል ይሆናሉ። የእኔ ልጆች መማራቸውን ካዩ ዘመዶቻቸው ይነቃቁና ይማራሉ። ሰዎች ትምህርት እንዲማሩ መበረታታት አለባቸው።

## የትራንስፖርት አብዮት

በሕይወቴ ካየኋቸው አንድና ዋነኛው ለውጥ [የቻይና መንገድ መሥራት ነው።] አካባቢያችን ኋላቀር አድርገውት ከቆዩት ነገሮች አንዱ የመገናኛ መንገድ እጦት ነው። በዚህም ምክንያት ብዙ ታሪካዊ ቦታዎች ከአንድ ውቅር አለት ድንጋይ የተሰሩ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት እንኳ ሳይቀር ለውጪ አለም ሳይታወቁ ቆይተዋል። እንዲሁም ደብረ አብኖረም፤ የጠቢቆት ገዳምና የኢማምግ ገዳም ሳይታወቁ ኖረዋል። አሁን ግን ለቻይና መንገድ ምስጋና ይግባውና በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ጉብኝዎች የላሊበላን አብያተ ክርስቲያናት በመቄት ወረዳ አድርገው ለመጐብኘት ሲመጡ እነዚህን ገዳማትም ይጐበኛሉ። ስለሆነም መንገዱ ልማት እንዲስፋፋ አመቺ ሁኔታን ፈጥሮልናል።

# የቃላት ፍቺ

ከአስረጂዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ሲደረግ ያጋጠሙ
አንዳንድ ቃላት ግልጽ ለማድረግ ማንኛውም ጥረት ተደርጓል ይሁን እንጂ ለሁሉም ቃላት ትክክለኛ ትርጉም ለመስጠት የሚቻ ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አንዳንዱ የአማርኛ ቃላት ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ወሎ አካባቢ ብቻ የሚነገሩ ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ሀጅ | ▪ | በእስላሞች ወደ መካ ኃይማኖታዊ ጉ አድርጐ ለመጣ የሚሰጥ ስያሜ፤ |
| ላዳን | ▪ | 30 ኪሎ ግራም ለመያዝ የሚችል ከበ ወይም ከፍየል ቆዳ የተሰራ ከረጢት፤ |
| መምሬ | ▪ | ቄስ ወይም መምህር፤ |
| ማኅበር | ▪ | ከህብረተሰቡ አንድ አይነት እምነ የሚከተሉ ሰዎች በቅድሳን ስ የሚሰባሰቡበት የኅብረት ግንኙነት፤ |
| ሰንበቴ | ▪ | በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚበላ የሚጠጣ ድግስ እየተዘጋጀ የሚቀርብበ የህብረተሰብ ማኅበር፤ |
| ሽሮ | ▪ | ተቆልቶ የተፈጨ ሽንብራ ወይም አተር |
| ቀበሌ | | የአካባቢ አስተዳደር የመጨረሻ እርከን፤ |
| ቀኛዝማችና | ▪ | ባህላዊ ወታደር የክብር ማዕረጐች፤ |
| ግራዝማች | | ወታደሩን የሚመሩ የነበሩ፤ |
| ቁራን | ▪ | የእስላሞች የተቀደሰ መጽሐፍ |
| ቁና | ▪ | 10 ኪሎ ግራም መያዝ የሚችል ከሰበዝና ከአክርማ የተሰፋ መስፈሪያ፤ |
| ቃዲ | ▪ | በእስላም የኃይማኖት መሪና ዳኛ፤ |
| ቅሬ | ▪ | ሰዎች ሲሞቱ በአባላቱ መዋጮ የቀብር ሥነ ሥርዓት የሚያስፈጽምና ለሃዘንተኞችም ምግብ መሠጠቱን የሚያረጋግጥ ባህላዊ ማኅበር፤ |
| በልግ | ▪ | በመጋቢትና በሚያዝያ ወራት አነስተኛ ዝናብ የሚጥልበት ወቅት፤ |
| ባንቡሌ | ▪ | በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ የበሽታ አይነት፤ |
| ብር | ▪ | የኢትዮጵያ ሕጋዊ ገንዘብ መጠሪያ፤ አንድ ብር ትንሹ የወረቀት ኖት ሲሆን |

| | |
|---|---|
| | 100 ማንቲሞች ያህል ነው። |
| ጠርጥም | ▪ በመስጊድ እስላሞች በየቀኑ ዐሎት ካደረሱ በኋላ በመሰባሰብ ቁርስ የሚያደርጉበት ሕብረት፣ |
| ቲን | ▪ ግማሽ ኪሎ ግራም እህል የሚይዝ ጣሳ፣ |
| ዛለር (ታላር) | ▪ የጥንት ገንዘብ ሳንቲም፣ |
| ኃይለስላሴ | ▪ ከ1920-1927 እና ከ1933-1966 ድረስ የነበሩ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት፣ |
| አረቄ | ▪ ከማሽላ/ ከዘንጋዳ ፣ ከዘንባባ/ቴምር ፍሬ የሚሰራ ጠንካራ አልኮል ያለው መጠጥ፣ |
| አቆማዳ | ▪ ከበግ ወይም ከፍየል ቆዳ የተሰራ ከ50-60 ኪሎ ግራም እህል መያዣ፣ |
| አውራጃ | ▪ በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ከክፍለ ሃገር ዝቅ ያለ ከወረዳ ከፍ ያለ የተወሰነ አካባቢ የሚይዝ የአስተዳደር እርከን፣ |
| ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ | ▪ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር፣ ከ1983 ጀምሮ በስልጣን ላይ ያለ (ከሽግግር መንግስት በኋላ በ1987 ምርጫ አካሂዷል) |
| ኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል | ▪ በአፍሪካ በረሃማ/ ቆላማ አካባቢዎች በልማት ላይ የሚሠራ ድርጅት |
| እልፍ | ▪ በሕብረተሰቡ ተራ በተራ የሚጦር ሽማግሌ ወይም አካለ ስንኩል የሆነ ሰው ማለት ሲሆን፣ በተራ ትርጉሙ ደግሞ ማንኛውም የሚያልፍ ሰው ማለት ነው፣ |
| እቁብ | ▪ ባህላዊ የብድርና የቁጠባ ማኅበር፣ |
| እንጀራ | ▪ የጤፍ ሊጥ በምጣድ የሚጋገር፣ ለምግብ የሚሆን፣ |
| እንግሊዝኛ | ▪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቻል የክብር እና የኩራት ምልክት ሆኖ ይታያል፣ |
| ወረዳ | ▪ ከቀበሌ ከፍ ያለ የአስተዳደር እርከን፣ |
| ደርግ | ▪ ከ19666-1983 የነበረ የኢትዮጵያ ወታደራዊ አገዛዝ፣ |
| ደገዛ | ▪ በወሎ በየቁጥቋጦው ተሸጉጠው እህል የሚያጠፉ ነፍሳት፣ |

| | |
|---|---|
| ድሪ | ▪ የትላትል ስብስብ (እህል/ አዝርዕት የሚያጠቃ) |
| ገና | ▪ የእየሱስ ክርስቶስ ልደት ማክበሪያ ጊዜ የሚደረግ ጨዋታ፤ በፈረንጆች ሆኪ እየተባለ የሚጠራውን የሚመስል፤ |
| ጋቢ | ▪ ከጥጥ ፈትል የተሰራ በብርድ ጊዜ የሚለበስ ሸማ፤ |
| ግሎባል | ▪ ሳሳካዋ-ግሎባል 2000 በጃፓን መንግስት ድጋፍ የሚካሄድ ብሔራዊ የግብርና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር፤ |
| ግሽርጥ | ▪ እግርና እጅን ለማስዋብ የሚጠቅም ስር ፤ (ለቅንጦት የሚገዛ) |
| ጠላ | ▪ በቤት ውስጥ የሚጠመቅ የአካባቢ የመጠጥ አይነት፤ |
| ጫት | ▪ ለማነቃቂያ እየታኘከ የሚወሰድ የእፅዋት ዓይነት፤ |
| ፌንጠራ | ▪ ፌንጣ፤ |

<u>እፅዋትንና አዝዕርትን በሚመለከት የተሰጡ የቃላት ፍቺዎች</u>

| | |
|---|---|
| ሳማ | ▪ እንደ ጐመን ተቀቅሎ የሚበላ እጽዋት፤ |
| አብሽ | ▪ ለዳቦና ለበርበሬ ቅመም የሚያገለግል የአዝርዕት አይነት፤ /Trigonella foenum-graecum/ |
| ወሰራ | ▪ በደጋማ አካባቢዎች የሚዘራ የብርዕ እህል፤ |
| ዳጉሳ | ▪ ለጠላ ቂጣ የሚያገለግል የእህል ዓይነት፤ /Eleusine coracana/ |
| ገንጭ/ እንክርዳድ | ▪ በእህል መሐል እንደ አረም የሚበቅል አጃ የሚመስል እጽዋት፤ /Avena fatua/ |
| ጊቲን | ▪ ሥሩ የሚበላ ዕጽዋት፤ |
| ጤፍ | ▪ ልሞ ተፈጭቶ ከተቦካ በኋላ ተጋግሮ እንጀራ በመሆን የሚበላ ደቃቅ የብርዕ እህል፤ /Eragrostis tef/ |

ሃይማኖት 26-27
ክርስትና 41፤42
እስልምና 47
(ማንነት፤ማኅበራዊ ተቋማት፤
ማኅበራዊ ግንኙነት
የሚለውን ይመልከቱ)
ልማት 52፤53
ሥልጠና 16 ፤18
መሬት 39
ክፍፍል 8-9፤18
ግጦሽ 7፤22-23 ፤ 39
ውርስ/ የመሬት ስሪት 20፤
23
ምርታማነት 23-24
እጥረት
(የመሬት መራቆትና ቤተሰብ
የሚለውን ይመልከቱ)
ማንነት 15 ፤ 74 ፤ 75
(ሃይማኖት የሚለውን
ይመልከቱ)
ማኅበራዊ ተቋማት 24 ፤25 ፤26 ፤32
ማኅበራዊ ግንኙነት
ለአዛውንትና ለአቅመ
ደካሞች የሚደረግ
እንክብካቤ 14፤56
ምግብ
አመጋገብ
የምግብ እጥረት 36
(መሬት፤ረሃብ የሚለውን
ይመልከቱ)
ረሃብ 58-59
የምግብ እርዳታ
ሰፈራ 76-77
ስደት 49
ሕዝብ 7፤38
የቤተሰብ እቅድ፤ የሕዝብ
እድገት
ሴቶች 10-12 ፤32 ፤82
የሥራ ጫና 62
(ጾታ የሚለውን ይመልከቱ)
ባህላዊ ልማዶች
ዘፈኖች 53-54
ታሪክ 65-66
የቤተሰብ መሬት የሚለውን
ይመልከቱ
ትምህርት 18-19፤31፤75
ሃይማኖት
ትምህርት ቤት
ማኅበራዊ ተጽእኖ
አንጥረኛ - አመለካከት 33፤60
ኢኮኖሚ
መሬት፤ ከብቶች፤ ሕዝብ
የሚለውን ይመልከቱ
እኩልነት 54-55 ፤ 82-83
ትምህርት፤ ጾታ፤ መሬት
የሚለውን ይመልከቱ
ከብቶች 22
ጤና/በሽታ
ድግስ/በዓሎች
ሀይማኖት፤ ማኅበራዊ
ተቋማት የሚለውን
ይመልከቱ
ግብርና 13፤23
እህል 37
ግብአት 20
መስኖ 12
ተባዮች 40
እርሻ በማረስ ምርት
መከፊል
(መሬት የሚለውን
ይመልከቱ)
ጤና 35
አመጋገብ 36፤37
አካለ ስንኩል
በሽታ 56-57
የጤና መገልገያዎች
መድሃኒት/ዘመናዊና ባህላዊ
መድሃኒቶች 31፤44
ጾታ አመለካከት/ ግንኙነት 62
የሥራ ክፍፍል/ኃላፊነት

ወጣቶች፣ ቤተሰብ፣ ጋብቻ
የሚለውን ይመልከቱ፡
ቤተሰብ
ታሪክ/የዘር ሃረግ ግንኙነት
ቅጥር
ስደት የሚለውን ይመልከቱ፡
የአየር ጠባይ 7፣8
ለውጥ
ድርቅ 49፣50፣76
የዝናብ መጠን 22
የመገናኛ አውታሮች 27-28፣34,83
ሬዲዮ 69
መንገድ ትራንስፖርት
የማኅበራዊ ድጋፍ፣ ማኅበራዊ
ግንኙነት ይመልከቱ፡
(ትምህርት፣ኃይማኖት
የሚለውን ይመልከቱ፡)
የአፈር ክለት/መሸርሸር 7
ዛፎች 21
የደን ምንጠራ 21
የዱር እንስሳት 21፣40
የቱሪስት መስህብ 35፣83
ገበያ/ ንግድ 71፣73
ጋብቻ/ ፍቺ 48፣53፣79